# ያልተቋዋጨ

ጅማሮው አለ በውስጤ ያልተቋዋጨ
ቀደምት ከታሪክ የመነጨ
ዛሬ አልታይ ብሎ የቀጨጨ

ከእምድር ከሰማይ የከበደ
ሰው በቁሙ ያነደደ
ስንቱን ያሰቀለ ያነደደ
ስንቱን በስለት ያሳረደ

ተቀብሮ አልወጣ ያለኝ
በውስጤ ሆኖ የሚነዘንዘኝ

ተነስ እያለ የሚቀሰቅሰኝ አለ ጅማሮ በውስጤ
ቀድሞ የተጀመረ በእነ አጤ
ከእንቅልፍ አባኖ መደንገጤ

እያንቀጠቀጠ አላላውስ ያለኝ
በውስጤ ተቀምጦ የሚነጨኝ
ሌት እንቅልፍ እየነሳኝ

አለ ጉድ በውስጤ ያልገባኝ
አያት ቅድም አያቴ የጀመሩት
ፅፈው አትመው ያስቀመጡት
እነሱም ጀምረው ያልጨረሱት

ለኔ በውርስ የተውልኝ
ሌት በእንቀልፌ የሚያናውጠኝ
ቀን በሜዳ የሚያባዝነኝ

ወገን ተነሱ እንቁዋጨው
ጅማሮው አለ እንጨርሰው
አፍሪካ ላይ ሲበራ የኖረው
ትውልዱን እንደቶን የበላው

የጥቁር አንገት ያቀና
ለሰው ልጆች ስብእና
ዛሬም ያልተቁዋጨው ያ ገናና
ዛሬ ቁዋጩት ተነሱና

እኔ ውስጥ ያለ እናንተም ውስጥ አለ
እያብከነከነ ስንቱን ያስገደለ

EthioLion.Com

ዛሬም በውስጣችን የበሰለ
ወደ ውስጥ እንጂ ወደ ውጭ አልበቅል ያለ

ይውጣና ይብቀል በምድሪቱ
ያሳረፈን እኛንም መወትወቱ
መለፍለፍ ይብቃ በአንደበቱ
ወጉ እንዲያ ነበር የጥንቱ

አሁን ምን ያደርጋል ግርግሩ
ቀናቱ አልፎ ሲመጣ ወሩ
እንዲያው ማውራት ሳይሰሩ
ሞልቶ ገንፍሎ ብድሩ

ወገን ይብቃን መግደርደሩ
ይከውን ይቁዋጭ በምድሪቱ
የአድዋው የማይጨው ቅሬቱ
ዘመኑ ሳያልፍ ወቅቱ
ስራችን ይታይ በምድሪቱ
ወገን ይብቃን መቆጨቱ

coventery 2009apr
ወንድወሰን ሰብስቤ
COVENTERY
2009apr

EthioLion.Com